Tape No. B4152, N.Z.,
12/94

መሠረት መጣል

በንስሃ ወደ እምነት መሄድ

ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤
ይህም ጸጋ÷ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን÷ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን÷ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤
መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን÷ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ÷ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።

እንግዲህ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሚያሳየንን አስባችሁ ከሆነ፤ለምን ክፋትን፤እና ኢፍትሀዊነትን እንዲሁም ረዘም ላለ ጊዜ መከራን ይታገሳል የሚል ጥያቄ ያስነሳ ይሆናል፤መልሱ እግዚአብሔር ሰዎችን ለራሱ ሊያደርግ ስለሚፈልግ ነው። ያ ነው ለዘመናችን የእግዚአብሔር የመጨረሻው ዓላማ።

አሁን“መሠረት መጣል ”ወደሚለው ሦስተኛው ትምህርት እንሄዳለን፤የዚህ መልዕክት ርዕስ “በንስሃ ወደ እምነት መሄድ” የሚል ነው።በመጀመሪያ መናገር የምፈልገው በንስሃ ካልሆነ በስተቀር ወደ እምነት የሚወስድ ሌላ መንገድ የለም። ወደዚያ ሊወስዳችሁ የሚፈልግ ሌላ ማንኛውም መንገድ ማታለል ነው። ያለ ንስሃ እውነተኛ እምነት ፈጽሞ የማይቻል ነው።

አሁን ተመልሼ አብረን እናጠናው የነበረውን በአጭሩ ልከልስ እወዳለሁ።በመጀመሪያ ደረጃ የክርስትና እምነት መሠረት የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።ስለዚህ እውነተኛ ክርስቲያን መሆን ያለበት ሰው ሁሉ እሱም ሆነ እሷ በዚያ መሠረት ላይ መገንባት አለበት። እኔ በኢየሱስ እና ጴጥሮስ መካከል የነበረውን ንግግር እንድትመለከቱ ነግሬአችኋለሁ፤ጴጥሮስ “አንተ ክርስቶስ መሲህ፤የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ”ብሎ የተናገረበት በተለየ መንገድ በእያንዳንዳችን ህይወት ላይ ምን መደረግ እንዳለበን የሚያሳይ ንድፍ ነው። እኔ በዚያ ግንኙነት አራት ፍሬ ሃሳቦች እንደነበሩ ተናገሬ ነበር።

ቁጥር አንድ፤ፊት ለፊት መጋጠም ነው፤ኢየሱስ እና ጴጥሮስ ፊት ለፊት ቆመው ነበር፤በመካከላቸውም ማንም አልነበረም፤ካህንም ሆነ ሌላ ሦስተኛ ወገን በመካከላቸው አልነበረም።

ሁለተኛ፤ስለ ኢየሱስ ዘለአለማዊ ማንነት በእግዚአብሔር መንፈስ የተሰጠ መገለጥ ነበር—ያም ስለ አናጺው ልጅ ሳይሆን፤ህያው ስለሆነው የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ሦስተኛ፤ጴጥሮስ ያንን መገለጥ ተቀብሎ እውቅና ሰጥቷል።እሱ አልቃወመም፤አምኖ ተቀበለ እንጂ።

በአራተኛ ደረጃ፤እምነቱን በሰው ፊት መስክሯል።

እነዚህ፤ሁሉም በእውነተኛ እና ስኬታማ በሆነ ክርስቲያን ሕይወት መሠረት ላይ ሊመሰረቱ የሚገባቸው ነገሮች እንደሆኑ አምናለሁ። ፊት ለፊት መግጠም፤መገለጥ፤እውቅና መስጠት እና በህዝብ ፊት መመስከር።

ስለሆነም ከዚያ በኋላ ይህን በጣም አስፈላጊ እና ጠቃሚ የሆነ ጥያቄን ተመልክተናል፤አንድ ጊዜ ይህንን መሠረት ከጣላችሁ፤እንዴት በእርሱ ላይ ትገነባላችሁ? እንዲሁም ኢየሱስ ባስተማረው የጥበበኛው እና ሞኙ ሰው ምሳሌ ላይ በዚህ መሠረት ላይ የሚገነባውን ህንጻ ተመልክተናል፤በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲሁም ኢየሱስን እንደ ሕያው ቃል መቀበል፤ከዚያም ኢየሱስ የተናገረውን መስማት እና ማድረግን ደግሞ የሚያካትት ነው። ስለዚህ፤ በመሠረቱ ላይ መገንባት ማለት ኢየሱስ የተናገረውን መስማት እና ማድረግ ነው።

እንግዲህ በቀደመው የትምህርት ክፍለ ጊዜአችን የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣንና ኃይል ተመልክተናል።ሥልጣን (authority) የሚለው ቃል ደራሲ (author) ከሚለው የመጣ መሆኑን ጠቁሜአለሁ። ስለዚህ፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን በጸሐፊው ይወሰናል። ጸሃፊው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው፤የእግዚአብሔር መንፈስ፤ራሱ እግዚአብሔር ነው።ስለዚህ የእግዚአብሔር ሥልጣን ያለው በመጽሐፍ ቅዱስ ዘንድ ነው።

ከዚያም፤ቃሉ በሁለት መልኩ እንደሚኖርን ጠቅሻለሁ፤እነሱም የተፃፈው ቃል እና የግል ቃል ናቸው፤የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ኢየሱስ ሥጋ ሆነ። ስለዚህ ይህን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ባለዎት የግል ግንኙነቶች ውስጥ አያይዘዋለሁ።እንዲህም እላለሁ፤ቃሉን ከምትወዱት በላይ እግዚአብሔርን ልትወዱ አትችሉም። ቃሉ የሚላችሁን ከምትታዘዙት በላይ እግዚአብሔርን ልትታዘዙ አትችሉም።እግዚአብሔር በህይወታችሁ ያለውን ስፍራ ለማወቅ ከፈለጋችሁ፤መጽሐፍ ቅዱስ በህይወታችሁ ያለውን ስፍራ ማወቅ ይጠበቅባችኋል፤ምክንያቱም ሁለቱም ተመሳሳይ ናቸውና።መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፉ የተቀመጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ኢየሱስ የእግዚአብሔር የግል ቃል ነው።በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በኩል የእግዚአብሔር የግል ቃል ወደ ህይወታችን ይመጣል።

እንግዲህ ዛሬ የእምነት አስተምርዎ ወይም የዶክትሪን መሰረት ላይ ወደማደርገው ውይይት መሄድ እፈልጋለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተመሠረተውን የግል መሰረት ተመልክተናል።ዳሩ ግን አዲስ ኪዳን ደግሞ የእምነት አስተምርዎ ወይም የዶክትሪን መሠረተ እንዳለ ያሳያል።ይህ በሚሊዮኖች ከሚቆጠሩ ክርስቲያኖች እውቀት ያመለጠ መገለጥነው፤ነገር ግን በዕብራውያን ምዕራፍ 6:1-3 በግልጽ ተቀምጧል። አሁን ወደዚያ እንመለሳለን።ዕብራውያን 6፡1-3፤ እንዲህ ይላል፤

ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ መሠረትን ደግመን አንመሥርት÷ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት÷ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን ስለ ሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው።
እግዚአብሔርም ቢፈቅድ ይህን እናደርጋለን።

Tape No. B4152, N.Z.,
12/94

አሁን ልታጣምሩት የሚገባችሁ ሁለት ሀሳቦች አሉ።በመጀመሪያ ደረጃ፤መሰረት መጣል አስፈላጊ ነው።

መሰረቱን ካልጣላችሁ ሕንፃውን መቼም መገንባት አትችሉም። ሆኖም አንድ ጊዜ መሰረት ከጣላችሁ በኋላ መሰረቱን እንደገና መገንባት የለባችሁም፤ነገር ግን፤ሙሉ ሕንፃውን ወደ መገንባት ልትሄዱ ይገባል።እነዚህ ሁለት የተጣመሩ ሃሳቦች ናቸው። እንግዲህ መሰረት ተብሎ በዕብራውያን 6፤1 የተቀመጠውን ትመለከታላችሁ።

ይህ የክርስትና እምነት ወይም ዶክትሪን መሰረት ነው፤እናም ስድስት አስተምርዎችን ወይም ዶክትሪኖችን ይዘረዝራል፤

ቁጥር አንድ፤ከሞተ ሥራ ንስሐ

ቁጥር ሁለት፤ በእግዚአብሔር እምነት

ቁጥር ሦስት፤የጥምቀቶች አስተምርዎች፤የብዙ ነው

ቁጥር አራት፤እጆችን መጫን

ቁጥር አምስት፤ የሙታን ትንሣኤ

ቁጥር ስድስት፤ዘላለማዊ ፍርድ

ይህን ከተከታተላችሁ ከክርስትና እምነት መነሻ ነጥብ አንስቶ እስከ ዘላለማዊ ፍፃሜው ሙላት ሲወስደን ትመለከታላችሁ። የክርስትና እምነት በጊዜ ሂደት እንደማይቋረጥ መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው፤በዚህ ህይወት ወይም በዚህ ዓለም አይቋረጥም። ከዚህ ዓለም ባሻገር አልፎ ይወስደናል።ከጊዜ ባሻገር ወደ ዘለዓለም ይወስደናል።እኔ ዛሬ በርካታ እጅግ በርካታ የሆኑ ክርቲያኖች ስለ ዘለዓለም ምንም አይነት ራዕይ የላቸውም ብዬ እፈራለሁ። ማንኛውም ጉዳዮች በጊዜ ሂደት እንደሚከሰት ያስባሉ። በእርግጥም፤ጳውሎስ፤በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፤ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን ይላል። ከጊዜ እና ዘለዓለም ባሻገር የሚወስድ ራዕይ ከሌላችሁ፤ሁኔታችሁ የሚያሳዝን ነው የሚሆነው፤እናም በጣም ብዙ ተስፋ አስቆራጭ ነገሮች ውስጥ ያልፋሉ፤ምክንያቱም ጊዜ ሙላት አይደለምና። ፍፃሜው በዘለዓለም ውስጥ ይመጣልና።

እንግዲህ እነዚህ ስድስት አስተምህሮዎች ወይም ዶክትሪኖች ንስሃ ከሆነው የመጀመሪያው ነጥብ ተነስቶ ወደ ትንሣኤ እና ፍርድ

ይወስደናል።

አሁን ስለመጀመሪያው መሠረተ ትምህርት በመናገር መጀመር እፈልጋለሁ።ያም ከሞተ ሥራ ንስሐ ነው። ነገር ግን መጀመሪያ ላይ አንድ

ነገር መጠቆም ይኖርብኛል፤አንድ በጣም ተጠቃሽ የሆነ ነገር በዕብ 6፡3 ላይ ይናገራል፤እግዚአብሔር ከፈቀደ ይህን እናደርጋለን።

እግዚአብሔር ከፈቀደ ወደ ሙላት እና ፍፃሜ እንሄዳለን። አሁን "እግዚአብሔር ለምን አይፈቅድም?" ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል።በእርግጥ ሁላችንም እንድንቀጥል ይፈልጋል። ከትንሽ እና ቀላል የህንጻ ምሳሌ ተነስቼ እመልስላችኋለሁ። ዛሬ በሰለጠነው ዓለም በየትኛውም ትልቅ ከተማ ውስጥ አንድ ሕንፃ ለመገንባት ዕቅድ ማውጣት አለባችሁ፤ከዚያም ከባለስልጣናት ፈቃድ ማግኘት ይኖርባችኋል፤እነሱም እቅድዎን ማፅደቅ አለባቸው።ከዚያም ህንጻውን በሚገነቡ ጊዜ መጥተው የህንጻውን ሁኔታ ደረጃ በደረጃ መቆጣጠር አለባቸው። በእርግጥ እነርሱ በመጀመሪያ የሚቆጣጠሩት መሰረቱን ነው፤ምክንያቱም መሠረቱ አስተማማኝ ካልሆነ ሕንፃው አስተማማኝ እንደማይሆን ያውቃሉና።የእርስዎ መሰረት ጠንካራ ካልሆነ ሕንፃውን ለመቀጠል ፈቃድ አይሰጡም።

እግዚአብሔር እናንተንም ሆነ እኔን እንድንረዳ የሚፈልገው በተመሳሳይ ነው። እንግዲህ እርሱ "መሰረታችሁን መቆጣጠር እፈልጋለሁ፤የመሠረታችሁት መሰረት በእኔ መስፈርት መሰረት የተገነባ ካልሆነ፤በግንባታው እንድትቀጥሉ ፍቃድ አልሰጣችሁም።" ይለናል።

በዚህ የክርስትና እምነት በሆነው የመጀመሪያ ትምህርት ያለ ምንም እድገት፤ወደ መጨረሻው የእድገት ምዕራፍ፤እንዲሁም ወደ ፍጻሜው ሳትደርሱ ለዘለዓለም መሄድ ትችላላችሁ፤ምክንያቱም ትክክለኛውን መሰረት አልጣላችሁምና።ስለዚህ ስለ ክርስትና እምነት መሰረት እነዚህን ስድስት አስተምርዎች በሚገባ ማወቅ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ተመልከቱ።

አሁን የመጀመሪያውን ከሞተ ሥራ ንስሃ የሚለውን እንመለከታለን። በመጀመሪያ የሞተ ስራዎች ምንድ ናቸው? አብዛኞቹ አዲስ ትርጉሞች ማንኛውም ወደ ሞት የሚመሩ ሥራዎች ወይም ተግባሮች የሞተ ስራ ይባላሉ ይላል። ያ ትክክል ነው ብዬ አላምንም። እኔ የሞተ ሥራ በእግዚአብሔር ላይ ባልተመሰረተ እምነት የምናደርጋቸው ማንኛውም አይነት ተግባር የሞተ ሥራ እንደሆነ አምናለሁ። ማንኛውም በእምነት ያልሆነ ሁሉ የሞተ ሥራ ነው። ለምናደርገው ሥራ ህይወት የሚሰጠው እምነት ነው። ስለዚህ ምናልባት ጥሩ ወደ ቤተክርቲያን የምትሄዱ ሰዎች ትሆናላችሁ፤ወይም ለድሆች ገንዘብን የምትሰጡ ትሆኑ ይሆናል፤ወይም የጸሎት ሰዎች ተብላችሁ ተጠርታችሁ ይሆናል፤ነገር ግን የምታደርጉት ሁሉ በእምነት ካልሆነ የሞተ ሥራ ነው።ማንኛውም በእምነት ካልሆነ ነገር መራቅ አለብን።ስለ ምናምነው እና ስለምንተገብረው ነገር ህይወትን የሚሰጠው እምነት ብቻ ነው።

ያ ማለት በኃጢያት ሕይወት እየኖራችሁ ነው ማለት አይደለም፤ሆኖም ግን ለእግዚአብሔር ህያው አልነበራችሁም ማለት ነው፤ ምክንያቱም እምነት ወደ ልባችሁ መጥቶ የእግዚአብሔርን ህይወት ወደ እናንተ ስላላመጣ ነው።

አሁን፤ንስሃ ምን እንደሆነ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው።ንስሃ ግምታዊ ስሜት አይደለም። ብዙ ጊዜ ሰባኪዎች ሰዎችን በስሜታዊ አስተሳሰብ ውስጥ እንዲሳተፉ እና ወደ ክርስቶስ እምነት ሲጠሯቸው ተመልክቻለሁ።ብዙውን ጊዜ ስሜት ይመጣል ምክንያቱም ስሜት እንደ ጉም የሚበን ነገር ነው፤እናም ብቻቸውን ይቀራሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው ንስሃ ስሜት ሳይሆን ወሳኔ እንደሆነ በአምሯችሁ ያዙ። ከስሜት የሚፈልቅ ሳይሆን ከፈቃድ የሚመነጭ ነውና። የሰዎችን ፈቃድ መድረስ የምንችል ከሆነ እና ፈቃዳቸውን መቀየር የምንችል ከሆነ፤ ዘላቂ የሆነ ለውጦችን ማየት እንችላለን። ዛሬ በቤተክርስቲያን ያለው ለውጥ ተብለው የሚጠሩ ሁሉ ዘላቂ የሆኑ አይደሉም ምክንያቱም በእውነት ፈቃዳቸውን አልቀየሩምና።እነርሱ ያላቸው ስሜታዊ ልምምድ ብቻ ነው፤ምናልባት ለጥቂት ሳምንታት፤ወራት ወይም ዓመታት ደስተኞች ሊሆኑ ወይም በጣም ጥሩ ነገር ሊሰማቸው ይችል ይሆናል፤ነገር ግን በስተመጨረሻ በዚያ የሄዱበት ሁሉ አይኖርም፤ምክንያቱም ፈቃዳቸው አልተነካምና።

አሁን፤ሁለት ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋዎችን እንመለከታለን፤ እነርሱም የግሪኩ አዲስ ኪዳን እና የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ናቸው። እያንዳንዳቸው ቋንቋዎች ለንስሐ የሚገባ ቃል አላቸው። ስለሆነም ሁለቱንም ቋንቋዎች በአንድ ላይ የምናደርጋቸው ከሆነ የንስሃን ሙሉ ትርጉም እናገኛለን። በግሪኩ ቋንቋ ውስጥ ያለው የግሪክ ቃል ስለ ንስሃ ሲናገር “ሃሳብዎን መቀየር”ተብሎ ተተርጉሟል፤ያም አስተሳሰብን ስለመቀየር የሚናገር ነው።ስለዚህ በመጀመሪያ፤ንስሀ ማለት ስለኖራችሁት ህይወት አዕምሮን መለወጥ ማለት ነው። እኔ እራሴን ለማስደሰት እና የራሴን ፈቃድ ለመፈጸም ስኖር ነበር። ከዛሬ ጀምሮ ግን አዳኜን ኢየሱስን ለማስደሰት እኖራለሁ፤ይህ በእርግጥ ወሳኔ ነው። አስቀድሜ እንደተናገኩት ይህ ስሜት አይደለም። ያለምንም ግልጽ የሆነ ስሜት ንስሃ ልትገቡ ትችላላችሁ፤ነገር ግን ፈቃዳችሁን ሳትቀይሩ ንስሃ መግባት አትችሉም።

እንግዲህ ሌላው በአይሁዶች ዘንድ የተለመደ የእብራይስጥ—ቃል ነው፤ምክንያቱም እነርሱ በጣም እውነተኛ እና የማያስምሉ ህዝቦች ናቸው።ንስሃን በተመለከተ የእብራይስጡ ቃል በግርድፉ “ሙሉ በሙሉ መዞር” ይለዋል። ጀርባችሁን ለእግዚአብሔር ሰጥታችሁ በተሳሳተ አቅጣጫ እየሄዳችሁ ሳለ፤ፊታችሁን ወደ እግዚአብሔር 180 ዲግሪ ዞራችሁ“እግዚአብሔር ሆይ፤እዚህ ነኝ፤ተናገረኝ፤የምትለኝን ሁሉ አደርጋለሁ” ትላላችሁ።

ስለዚህ ሁለቱን በአንድነት በማድረግ ስለ ንስሃ ሙሉ የሆነ ስዕል ይኖራችኃል።እንግዲህ እምነት የሚመጣው ከንስሃ በኃላ ብቻ ነው። ጠቅላላው የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት በዚህ ቅደም ተከተል የሚሄድ ነው፤ያም ንስሃ መግባት እና ማመን ነው።ከእምነት ጋር የሚታገሉ በርካታ ሰዎች አሉ፤እንዳንዶቹም ዛሬ ጠዋት በዚህ ትገኛላችሁ።እውነታው ለእምነት

እየታገላችሁ አይደለም፤ንስሃ የሚጠይቀውን ሁኔታ ፈጽሞ አላሚችሁም። አያችሁ፤ከስድስቱ ዶክትሪኖች የመጀመሪያዎቹ ናቸው። ለምትገነቡት ህንጻ ተገቢ የሆነ መሰረት ካልመሰረታችሁ፤ህንጻችሁ የሚናወጥ ይሆናል።

ባለፉት አመታት በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን፤ለአማኞች በግል ስላጋጠሚቸው ችግሮች ምክር ሰጥቻለሁ።ከበርካታ የግል ተሞክሮዎች በኋላ ወደ እዚህ ድምዳሜ ደርሻለሁ፤ያም በግልጽ ከታወቁት—ወይም እውነተኛ—ክርስቲያኖች መካከል ያሉት ችግሮች ቢያንስ 50 በመቶ የሚሆኑት ፈጽሞ ከልብ ንስሃ ካለ መግባት እውነታ ጋር የተያያዘ ነው።እነሱ በፍጹም በሃሳባቸው አልተለወጡም። በእርግጥ እውነተኛ ውሳኔ አልወሰኑም።ሕይወታቸውን ለኢየሱስ ጌትነት አሳልፈው አልሰጡም፤እነርሱ እስካሁን "አሁን ይህን ባደርግ ለእኔ ምን ይጠቅመኛል?፤እኔ አሁን ያንን ባደርግ ምን እጠቀማለሁ?" ከሚል ነጥብ ተነስተው ነው ውሳኔዎችን ለመወሰን እያሰቡ ያሉት።ንስሃ በገባችሁ ጊዜ፤በዚያ መንገድ አታስቡም።"ይህንን ባደርግ፤ኢየሱስ ይከብራልን?"ብላችሁ በዚህ መንገድ ማሰብ አለባችሁ። በሁለት ሃሳብ የሚያነክሱ እጅግ በርካታ የሆኑ ሰዎች አሉ—በተለይም ወጣት የሆነው የህበረተሰብ ክፍል፤ይሁን እንጂ በሁለት ሃሳብ መመላለስ የወጣቶች ችግር ብቻ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ሃሳብ የሚያነክስ ሰው በህይወቱ በተረጋጋ ሁኔታ እንደማይኖር ይናገራል። እሱ ጠንካራ የሆነ መሰረት ሊኖረው አይችልም፤እሱ ቋሚ የሆነ ህንጻ ሊኖረው አይችልም።

ስለዚህ አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች በጥሞና በማሰብ "በእርግጥ እውነተኛ ንስሃ ገብቼ አውቃለሁን? ወይስ አሁንም በሁለት ሃሳብ የማነክስ ነኝ? ወይም ደግሞ የሰኞ ዕለት ዓላማዬ ኢየሱስን ማስደሰት ነው፤የማክሰኞ ደግሞ ራሴን ማስደሰት ነው።"ብላችሁ እራሳችሁን በመጠየቅ ወዴት እንዳላችሁ እንድታውቁ እጋብዛችኋለሁ።አያችሁ፤በእውነቱ፤በጣም የከፉ ሁለት ዓለሞችን አሉን። በዚህ ዓለም ስትኖሩ በሁለት ሃሳብ እያነከሳችሁ እና፤በሁለት ማንነት ሆናችሁ ለራሳችሁ ብቻ መኖር ማቆም አለባችሁ።

አሁን ወደ ንስሃ ተፈጥሮ መሄድ አለብን።ኢየሱስ እውነተኛውን ንስሃ የሚያንፀባረቅ በጣም ግልፅ እና ፍጹም የሆነ ምሳሌ ሰጥቷል። ያም የጠፋው ልጅ ምሳሌ ብለን የምንጠራው ነው። እንድ ሰው መልካም አባት ተብሎ መጠራት አለበት ሲል ነበር። ታሪኩን በሉቃስ 15 ውስጥ የምታስታውሱት ነው፤አብዛኞቻችሁ ታውቁታላችሁ።የባለጸጋው ቤተሰብ ሁለተኛ ልጅ አሁን ከአባቱ ሁሉንም ውርስ ለመውሰድ ወሰኖ ወደ ሩቅ ሀገር ሄዶ ለመኖር ተነሳ። እርሱ ሁሉንም ዓይነት ኃጢአቶች ያደርግ ነበር።ከዚያም ከአባቱ የወሰደውን ውርስ ሁሉ ከጨረሰ በኋላ ረሃብ መጣ እናም በዚያ ሊያገኘው የቻለው ብቸኛው ስራ አሳማዎችን መመገብ ነበር። እንግዲህ ማስታወስ ያለባችሁ፤እሱ አይሁድ ስለነበር፤ለእርሱ አሳማዎችን መመገብ በጣም ዝቅተኛ የሆነ የውርደት ስራ ነበር—ከአሳማ አርቢዎቹ ጥቂት እንኳን ሊያገኝ አልቻለም። ስለ እነርሱ አንዳች እየተናገርን ሳይሆን በአይሁድ ህዝብ ዘንድ ያለ ነው፤አሳማዎች የሚሆኑት በውጪ ነውና።

Tape No. B4152, N.Z.,
12/94

እንግዲህ እሱ እዚህ ነው፤የለበሰው ቁራጭ ጨርቅ ነው፤አሳማዎችን እየመገበ ይገኛል፤በጣም ተርቧል፤አሳማዎቹ ከሚበሉት ሊጠግብ ይመኝ ነበር። በሉቃስ 15፤17 የሆነው ይህ ነው፤

“ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ. . .” ይላል፤ ልትመጡበት የሚገባ ነጥብ እዚህ ጋር ነው። ወደ ልባችሁ *መመለስ* አለባችሁ፤የእውነት ሰዓት ብዬ እጠራዋለሁ። እውነተኛ ማንነታችሁን *መመልከት* አለባችሁ። እግዚአብሔር እራሳችሁን እንደሚመለከታችሁ እራሳችሁን *መመልከት* አለባችሁ።

“ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ፦ እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ።
ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና፦ አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥
ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ። ”

አሁን ሁለት ነገሮችን ትመለከታላችሁ?—ምክንያቱም እንዲህ ይላል፡

“ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ።”

እሱ ውሳኔ ወስኖ ተመለሰ።ንስሃ ማለት ያ ነው። ውሳኔ *መወሰን* እና በውሳኔአችን *መመላለስ* አለብን። ወደ አሳዘናችሁት እና፤ወደሚወዳችሁ አባት እግዚአብሔር በመሄድ፤ “ህይወቴን አመሰቃቅያለሁ፤የራሴን ህይወት መምራት አልችልም፤ታስፈልገኛለህ፤እንደገና ትቀበለኛለህን?” ብለን በፊቱ መቅረብ አለብን። ለአባቱ ሊነግረው ያቀደው አስደናቂው ነገር “ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ።” የሚል ነበር።ነገር ግን በጀመረ ጊዜ፤አባቱ ይመለከተው ነበር።ይህ አጅግ አስደሳች እንደሆነ አስባለሁ።አባት እግዚአብሔር የሚሆነው እንደዚያ ነው። *መመለስ* ስንጀምር፤ይመለከተናል፤ይጠብቀናልም።

“እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው።”

እግዚአብሔር እንዲህ ነው። እሱ የሚያገኝን እንደዚህ ነው።

*“አንገቱን አቀፈውና ሳመው።”*ይላል።

“ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ። ” የሚሉትን የመጨረሻዎቹን ቃላቶች እንዲናገር አልፈቀደለትም።

ያ የእውነተኛ ንስሃ ውጤት ነው።በእግዚአብሔር ለመጎብኘት የዚህ አይነት ንስሃ መግባት ያስፈልጋል። ያ ነው ትክክለኛው ስዕል። እስቲ ለራሳችሁ ለአፍታ አስቡ።ወደ ራሱ ሄደና እንዲህ አለ “ህይወቴን አመሰቃቅያለሁ፤አባቴ የሰጠኝን ሁሉ አባክኛለሁ። ነገር ግን አሁን ውሳኔ እወስናለሁ። እመለሳለሁ፤ወደ አባቴ ቤት እመለሳለሁ፤እንዲህም አላለህ አዝኛለሁ”

Tape No. B4152, N.Z., 12/94

እሱም ተመለሶ ሄደ። ስለዚያ አስቡ። ያ እውነተኛ ንስሃ ነው። ንስሃ ተግባር ነው።

እንዲሁም ሃሰተኛ ንስሃ ብለን የምንጠራው የይሁዳ አይነት ንስሃ አለ፤በማቴዎስ 27 ላይ ተብራርቶ ተቀምጧል፤ቁጥር 3 እንደሚከተለው ይነበባል

በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ ተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ÷ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌች መልሶ÷
ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ ግን÷ እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ።
ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ።

ይሁዳ ይጸጸተ እንጂ አልተለወጠም ነበር።በእርግጥ፤እሱ የሚለወጥበትን ነጥብ አልፏል ብዬ አምናለሁ። ይህ ለእኔ አሳሳቢ ነው።ሰዎች በዚህ ህይወት ውስጥ ሊለወጡ የሚችሉበትን ቦታ ሊለቁ ይችላሉ። በሰው ልጅ ህይወት ውስጥ በጣም ትርጉም የለው ሰዓት እግዚአብሔር ንስሀ ትገቡ ዘንድ ሊነግራችሁ የሚጀምርበት ጊዜ እንደሆነ አስባለሁ። ትከሻችሁን እየነቀነቃችሁ "እኔ ፈቃደኛ አይደለሁም፤ምናልበት በኋላ" ልትሉ ትችላላችሁ። እግዚአብሔር እንደገና ያንን የንስሃ ጊዜ እንደሚሰጣችሁ ዋስትና የለም። በሰው ህይወት ውስጥ ለንስሃ ወሳኙ ሰዓት እግዚአብሔር መጥቶ "ንስሃ ግቡ፤እኔ ልመልሳችሁ ፈቅጃለሁ፤እወዳችኋለሁ" የሚልበት ሰዓት ነው።

እኔ በሰዎች ህይወት እና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመለከትኩትን አስተውያለሁ።እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ እና ጸጋውን የሚያግፋፋ አንድ ነገር እንዳለ ድምደሜ ላይ ደርሻለሁ። እሱ ጸጋውን በነጻ ለእኛ አቅርቧል፤ነገር ግን እኛ ለመቀበል የምናግፋፋ ከሆነ በእርግጥ ይቆጣል። በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ጸጋ የግፋፋ አንድ ሰው አለ። ስሙን ማን እንደሆነ ታውቁታላችሁን? ኤሳው ይባላል። እሱ በዕብራውያን 12 ላይ በሚገባ ተብራርቶ ተቀምጧል። ያንን ምንባብ ለአፍታ መመልከት እፈልጋለሁ፤ምክንያቱም እንደ እኔ እና እናንተ ባሉ ሰዎች ውስጥ ብዙ ኤሳዎች አሉና። ኤሳው ውሳኔአችንን እንደይወስን ሁላችንም መጠንቀቅ አለብን።ይህ ነው በዕብራውያን 12 ላይ የሚናገረው፤

ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፤ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።

ያለ ቅድስና ማንም እግዚአብሔርን ሊያይ እንደማይችል አስተውሉ።

የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው÷ ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ÷ ሴሰኛም

የሚሆን እንዳይገኝ÷ወይም ስለ አንድ መብል በኵርነቱን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ።

አሁን ኤሳው እርኩሰት እንደፈጸመ ምንም የተመዘገበ ማስረጃ የለንም፤ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ፊት ኤሳው የነበረው አመለካከት እርኩሰትን እንደመፈጸም የከፋ ነበር። የእርሱ አመለካከት ምንድ ነበር? ለአንድ ሰሃን የምስር ወጥ

Tape No. B4163, N.Z.,
12/94

ብኩርናውና አሳልፎ ሰጠ።እሱ እንደ በኩር ልጅ የብኩርና መብት ነበረው። የእርሱ ውርስ የነበረው ሁሉ ተወሰደ። ዳሩ ግን እርሱ በጣም ተርቦ ነበር፤እናም የዕቆብ ሰርቶት የነበረውን እጅግ ጣፋጭ የሆነውን የምስር ወጥ አሸተተ—ይህ ለእኔ ምን እንደሆነ ግልጽ ነው፤ምክንያቱም በአንድ ወቅት አረቦች መካከል ኖሬአለሁ፤በእውነቱ እነርሱ በትክክል ያዕቆብ ያዘጋጀው አይነት ጣፋጭ ወጥ የዘጋጃሉ፤ቆንጆ የምስር ወጥ፤የአረብ ሰርአቢት አዲስ ብለው ይጠሩታል። በጣም ጣፋጭ የሆነ ጣዕም አለው። ቤትን ያውዳል። ኤሳው ከአደን ደክሞት እና ተርቦ መጥቶ ያ ጠፋጭ የምስር ወጥ በሸተተው ጊዜ የነበረውን አጋጣሚ በአዕምሮዬ እስለዋለሁ። ተደራዳሪ የነበረው የዕቆብ እንዲህ አለ፤“ስማ፤ ብኩርናህን ትሸጥልኛለህ፤ከዚያም እኔ ይህን ጠፋጭ የምስር ወጥ እሰጥሀለሁ” ኤሳው አሁን ብኩርናዬ ምን ያደርግልኛል፤እኔ ተርቤአለሁ፤የቀረበልኝን እወስዳለሁ።” ብሎ ያሰበውን መገመት እችላለሁ፤ ኤሳው ብኩርናውን አግፋፋ፤እግዚአብሔርም በእሱ ተቆጣ። በኋላም እግዚአብሔር በነብዩ ሚልኪያስ “ያዕቆብን ወደድሁ፤ኤሳውን ጠላሁ” ይላል። ያ በጣም ጠንከር ያለ ሃሳብ ነው። የእግዚአብሔርን ጸጋ እና በክርስቶስ ኢየሱስ የቀረበላችሁን ውርስ ሆን ብላችሁ የምታግፋፉ ከሆነ እና ርካሽ እና ጊዜያዊ ወደ ሆነው የዓለም ደስታ የምትቀይሩት ከሆነ አግዚአብሔርን ታስቆጡታላችሁ።

> እናም እንዲህ በማለት ታሪኩን ይቀጥላል፡
>
> ከዚያ በኋላ እንኳ በረከቱን ሊወርስ በወደደ ጊዜ እንደ ተጣለ ታውቃላችሁና፤ በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሐ ስፍራ አላገኘምና።

አሁን የግሪኩ ግልጽ ያደርገዋል።እሱ የንሰሃን ስፍራ እየፈለገ አልነበረም፤እሱ እየፈለገ የነበረው በረከትን ነው። እሱ ተቀባይነት ሊያገኝ

አልቻለም፤ምክንያቱም ስፍራ አላገኘም ነበርና፤እንደገና የንስሃ እድል አላገኝም። በዚህ ህይወት ውስጥ አንድ ሰው የንስሃን ስፍራ

እንደሚያልፈው እና እንደገና ያንን እድል እንደማያገኝ አምናለሁ።ይህን ላስገነዝባችሁ እወዳለሁ፤ይህ እጅግ ጠንከር ያለ ሃሳብ ነው።

ዛሬ በብዙ ጉባኤ እና የሐይማኖት አስተምርዎ ስለ ንስሃ አስፈላጊነት ብዙ ይናገራል።ነገር ግን ያለ እውነተኛ ንስሃ እውነተኛ የሆነ እምነት

ሊኖር አይችልም።ሁልጊዜ የሚኖራችሁ የሚናወጥ እና የሚወድቅ ልምምድ ነው፤ምክንያቱም የመጀመሪያ መሰረት የሆነውን ንስሃ በሚገባ

አልጣላችሁምና፤ራስህን ከማስደሰት መዞር እና የራስን መሻት ከመፈጸም ወደ እግዚአብሔር መመለስ፤ወደ እግዚአብሔር ፊትን ማዞር፤

እና “እግዚአብሔር ሆይ፤እዚህ ነኝ። ማድረግ የለብኝን ንገረኝ፤እኔም እታዘዛለሁ።”ማለት ያስፈልጋል።

እውነተኛ ንስሃ ማለት ይህ ነው።

ዛሬ በዚህ እውነተኛ ንስሃ ያላደረጋችሁ ሰዎች አላችሁ። ለብዙ ችግሮቻችሁ ምንጭ እንደሆኑ ልነግራችሁ እወዳለሁ።

ልምምዳችሁ አንዴ የወጣ አንድ ጊዜ ደግሞ የወረደ ነው። አንድ ቀን ጥሩ ስሜት ይሰማችኋል፤በቤተክርስቲያን ውስጥ

ድንቅ የሆነ ህብረት ታደርጋላችሁ፤እንዲሁም ድንቅ እንደሆነ ታስባላችሁ።በሚቀጥለው ማለዳ አንድ ሌላ ነገር

ይከሰታል፤ከዚያም ስሜታችሁ ይወርዳል። እውነታው የመጀመሪያውን መሰረት በሚገባ ስላልጣላችሁ ነው። እናንተ

የገነባችሁት አንድ ቀን የሚናወጥ እና የሚፈርስ ህንጻ ነው።

አሁን ንስሃ ከእምነት ቀድሞ እንደሚሄድ አጽንኦት ሰጥቼ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። ያለ ንስሓ እውነተኛ እምነት የለም።ይህ በአዲስ

ኪዳን ውስጥ በሚገባ ተጠቅሷል። በማቴዎስ ምዕራፍ 3፤የመሲሁ ኢየሱስን መንገድ አስቀድሞ እንዲጠርግ ስለተላከው መጥምቁ

ዮሐንስ እናነባለን። እንግዲህ በአንድ ቃል የሱ መልዕክት የነበረው ምንድ ነበር? ንስሃ የሚል ነበር። በሌላ አነጋገር፤ መሲሁ

ከመምጣቱ በፊት ንስሃ አስፈላጊ ነበር ማለት ነው።ንስሃ ለመሲሁ መምጣት መንገድ የሚጠርግ ነው። የእግዚአብሔር ህዝብ

የነበረው እስራኤል በዚህ በንስሃ ልምምድ እስኪያልፉ ድረስ መሲሐቸውን ለመቀበል ዝግጁ አልነበሩም። ማቴዎስ 3:1–3 እንዲህ

ይላል

በዚያም ወራት መጥምቁ ዮሐንስ፦ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ ብሎ በይሁዳ ምድረ በዳ እየሰበከ መጣ። በነቢዩ በኢሳይያስ፦ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና።

እሱ የጌታን መንገድ እንዴት አስተካከለ? የእግዚአብሔርን ህዝብ ንስሃ እንዲገባ በመጥራት። ንስሃ ጌታ ወደልባችን እና ህይወታችን

እንዲመጣ የምናዘጋጅበት ብቸኛው መንገድ ነው።

መጥምቁ ዮሐንስ ይህን ተልዕኮ በጨረሰ ጊዜ፤ኢየሱስ ራሱ የዮሐንስን ትንቢታዊ ቃል ለመፈጸም፤የወንጌልን አገልግሎት ለመቀጠል መጣ።

በማርቆስ 1:14–15 እንዲህ ይላል፤

> ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እየሰበከና፦ ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ።

ንስሃ ግባ እና አመን። መጀመሪያ ንስሃ ከመግባታችሁ በፊት በእውነት ልታምኑ አትችሉም። ከኢየሱስ አንደበት የወጣው የመጀመሪያው

የትዕዛዝ ቃል ንስሃ ግባ እንጂ አመን የሚል አይደለም።

አስታውሳለሁ፤በደቡብ ምስራቅ እስያ በአንድ ስብሰባ ላይ ሳለሁ፤አንድ ሰባኪ የፈውስ መልዕክት ያስተላልፍ ነበር። አስደናቂ በሆነ የንግግር ችሎታው እግዚአብሔር ፈውስን በተመለከተ ስላለው ፈቃድ እና እቅድ ይናገርና፤ስለ ፈውስ የተሰጡ የተስፋ ቃሎችን እየጠቀሰ የስተምር ነበር። ነገር ግን ስለ ንስሃ አንድም ቃል አልተናገረም ነበር። ከዚያም ህዝቡ ወደፊት እንዲመጣ ጠራ፤አብዛኞቹ የባእድ አምልኮ የኃላ ታሪክ የነበራቸው ነበሩ፤ሆኖም እግዚአብሔር ያቀረበላቸውን ለመቀበል ምንም እውቀቱ አልነበራቸውም ነበር። ስለሆነም እነርሱን በማማከር እኔ እና ሩት በአንድነት ተሳተፍን።ያ ለእኔ ትልቅ ትምህርት ነበር። በነበረው መልካም ሃሳብ እና ይጠቀምበት በነበረው አስደናቂ የንግግር ችሎታ ህዝቡን ግራ አጋብቶት ነበር፤ምክንያቱም እሱ ያለ ንስሃ ወደ እግዚአብሔር ሊመጡ የሚችሉበትን መነሳሳት ሰጥቷቸው ነበር።በመልዕክቱ አንድም ንስሃ የሚል ቃል አልተጠቀመም ነበር።ይህን የምለው ሰባኪውን ለመተቸት አይደለም፤እኔ ይህን የምለው፤ትምህርት ስለወሰድኩ እና በርካታ እጅግ በርካታ የሆኑ ሰዎች አያሌ በሆነ ጥቅስ፤የወንጌል አብያተ ክርስቲያናት እና የወንጌል አገልግሎት ውስጥ ግራ ተጋብተው የተቀመጡ ስላሉ ነው፤ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊሰጣችሁ ያለውን በረከት ሁሉ ይነገራችኋል፤ዳሩ ግን እግዚአብሔር ከእናንተ የሚፈልገውን አይነገሯችሁም። የመጀመሪያው እሱ ከእኛ የሚፈልገው ንስሃ ነው።ሃሳባችሁን ቀይሩ፤180 ዲግሪ በመዞር ፊታችሁን ወደ እግዚአብሔር መልሱ፤እንዲህ በሉ "እግዚአብሔር ሆይ፤ምን ማድረግ እንደለብኝ ንገረኝ፤እኔም እታዘዘለሁ፤" ንስሃ ማለት ያ ነው።

አሁን የኢየሱስን የመጨረሻ አገልግሎት ከተመለከትን፤ የእርሱ መልዕክት መቼም ተቀይሮ አያውቅም። በሉቃስ 24፤ከትንሳኤው በኃላ፤ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ መመሪያን ሰጣቸው። በሉቃስ 24:46–47 የተነገረውን አስታውሱ፤ ይህ የሆነው ከትንሳኤው በኃላ ዓለምን ለቆ ከመሄዱ በፊት ነበር።

እንዲህም አላቸው፦ ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥
በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል።

ይህን መልዕክት አስተውሉ፤ንስሓ ማለት ከሐጢያት መዋጀት ወይም የሐጢያት ይቅርታ ማግኘት ነው። ዳሩ ግን ያለ ንስሐ የሚደረግ

ምንም አይነት የሐጢያት ይቅርታ አይኖርም፤ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአለም ላይ የሚሰበከው መልዕክት ይህ ነው። ንስሃ፤ከዚያም በስሙ

የሐጢያት ይቅርታ ይደረጋል።

በጴንጤ ቆስጤ ቀን ቤተክርስቲያን ወደ ህዝብ እይታ በመጣች እና ታላቅ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ በነበረበት ጊዜ እጅግ በርካታ

አይሁድ ተሰብስበው የሚሆነውን ለማወቅ ፈለጉ፤እናም ጴጥሮስ ቆሞ በሐዋሪያት ስራ ምዕራፍ 2 ላይ በጣም ታዋቂ የሆነውን ስብከት

ሰበከ። በመጨረሻም አምነው ጴጥሮስን እንዲህ አሉት፤ “ምን ማድረግ ይገባናል?”፤ይህ ቤተክርስቲያን በሐጢያተኞች የተጠየቀችው

የመጀመሪያው ጥያቄ ነው።እስቲ ይህን ክፍል ላንብላችሁ፤ ሐዋ 2:37

> ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ÷ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት÷ ወንድሞች ሆይ÷ ምን እናድርግ? አሉአቸው።

እንግዲህ እግዚአብሔር ምን እንድታደርጉ እንደሚፈልግ እና እናንተ ደግሞ ለመታዘዝ ፈቃደኛ በመሆን ወደምትፈልጉበት ስፍራ የምትመጡ ከሆነ እግዚአብሔር ስለሚፈልገው ነገር በጥርጣሬ ውስጥ አይተዋችሁም። እርሱ የሚያስቸግረው ለእናንተ መናገር ሳይሆን፤የሚስቸግረው እናንተ ልትሆኑ ወደምትፈልጉበት እና የምትታዘዙበት ስፍራ ማምጣት ነው።እነዚህ ሰዎች በሐጢያት ወቀሳ ውስጥ በሆኑበት ቅጽበት ለሐዋሪያቱ ተናገራቸው፤እነርሱም “ወንድሞች፤ምን እናድርግ?”አሉ። ጴጥሮስም እንደ እግዚአብሔር ቃል አቀባይ እና ቤተክርስቲያን በጣም ግልጽ፤ትክክል፤እና ተግበራዊ የሆነ መልስ ሰጣቸው።

> ጴጥሮስም “ንስሃ ግቡ” አላቸው።

መጀመሪያ የሚቀድመው ምንድ ነው? ንስሃ ነው ካላችሁ ትክክል ነው።

> ጴጥሮስም÷ ንስሐ ግቡ÷ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።

ሦስት የተስፋ ቃል ደረጀዎች አሉ

ቁጥር አንድ፤ንስሐ መግባት

ቁጥር ሁለት፤የውኃ ጥምቀት መውሰድ

ቁጥር ሦስት፤መንፈስ ቅዱስን መቀበል።

የእግዚአብሔር መርሃ ግብር ተለውጦ ያውቃል ብዬ አላምንም።እግዚአብሔር ዛሬ ኃጢአተኞች በትክክል እንዲያደርጉት የሚፈልገው ይህ እንደሆነ አምናለሁ።አብያተክርስቲያት ንስሃ ግቡ፤የውሃ ጥምቀት ውሰዱ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ተቀበሉ የሚለውን መልዕክት ሊያውጁት እንደሚገባ አምናለሁ።

ይህ መልዕክት በሚሰበክበት ስፍራዎች ሁሉ ላይ በጴንጤ ቆስጤ ቀን እንደሆነው በትክክል ይሆናል። ሰዎች ንስሃ ይገባሉ፤ይጠመቃሉ፤እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን ይቀበላሉ።እኔ ይህ ሲሆን ለበርከታ ጊዜ ተመልክቻለሁ፤ለበርካታ ጊዜ

Tape No. B4152, N.Z.,
12/94

ከውኃ በሚወጡ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ተመልክቻለሁ።ለምን መልዕክቱን ቀለል አድርገን አናቀርበውም?ያንን የማድረግ ምንም ስልጣን የለንም። የእኛ ብቸኛ ስልጣን የአዲስ ኪዳን መልዕክት የሆነውን ንስሃ ግቡ፤የውኃ ጥምቀት ውሰዱ፤መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ የሚለውን ማወጅ ብቻ ነው። መልዕክት በምናስተላልፍበት ጊዜ፤እግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣል።ለውጥ ያመጣው እግዚአብሔር አይደለም፤ለውጥ ያመጣው መልዕክቱ አይደለም፤ነገር ግን በበርካታ ጉዳዮች ለውጥ ያመጠችው ቤተክርስቲያን ናት።

ምናልባት ሊያስደነግጣችሁ የሚችል አንድ ነገር ልንገራችሁ፤ነገር ግን የውኃ ጥምቀት ሳይወስድ ደህንነትን ያገኘ ሰው ከሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ላገኝ አልችልም። እስቲ የምታገኙ ከሆነ ተመልከቱ።ምክንያቱም ኢየሱስ "ያመነ፤የተጠመቀ ይድናል።"ይላልና። እናንተ የሚኖራችሁ መብት ምንድ ነው፤ወይስ"የተጠመቀ"የሚለውን ቃል ልታውጡት ነውን?፤ደህንነት ማመን እና መጠመቅ ነው።ያንን በምታደርጉ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ታጭታችኋል ማለት ነው። ያ የቤተክርስቲያን መልዕክት ነው፤እንደ እግዚአብሔር ሐሳብ መቼም የሚቀየር አይደለም።

እንግዲህ የጳውሎስን አገልግሎት እንመልከት፤እርሱ ታላቁ የአህዛብ ሐዋሪያ ነው። ይህም በሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ላይ ተመዝግቦ

እንደተቀመጠ እንመለከታለን። በመጀመሪያ ጳውሎስ የሄደው በጣም የተማሩ ሰዎች እና የጣዖት አምላኪዎች ወዳሉባት ግሪክ ነበር።

እሱ በዚያ ያለውን አገልግሎት ለእነርሱ በመስበክ አጠናቀቀ። ያንን የማድረግ ሀሳብ ነበረው ብዬ አላስብም፤ይሁን እንጂ ያመነውን እነርሱ

ሊያውቁ በሚፈልጉበት ስፍራ ላይ አጠናቀቀ፤እናም ይናገራቸዋል፤እግዚአብሔርን ባለማወቅ እና ጣዖታትን በማምለክ ስላሳለፉት ጊዜያት

በመናገር መልዕክቱን በሐዋሪያት ሥራ 17፤30 ያጠናቅቃል፤ እንዲህ ይላል፡

እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤

ያ ንግግር ግልጽ ነው፤እግዚአብሔር በማንኛውም ስፍራ ላይ የሚገኙ ሰዎች ንስሃ እንዲገቡ ያዛል።ያ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የደነገገው ዓለም አቀፍ ህግ ነው። እኛ በንስሃ የምንመለስ ከሆነ ያለፈውን ሐጢያታችንን ሊረሳ ፈቃደኛ ነው።

እንዲህ ይላል:

ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለውና፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል።

ሌላው ብዙ ጊዜ የተጠቀሰው የሐዋሪያት ልዩ መልዕክት ኢየሱስ አዳኝ ብቻ ሳይሆን ፈራጅም ደግሞ እንደሆነ የሚያሳይ

መሆኑን አስተውሉ። እሱ ዘለዓለማዊ ደህንነትን በመስጠት ሙሉ እና ብቁ እንደመሆኑ መጠን በፍርድ ደግሞ እንዲሁ ነው። እርሱን እንደ ግል አዳኝ አድርጋችሁ ካልተቀበላችሁ፤በፍርድ ታገኙታላችሁ።ይህን ከብዙ ስብከቶች የተዘለለ ጉዳይ ነው።ሰዎች ሰለ አዳኙ ያወራሉ፤ነገር ግን ስለ ፍራጁ ምንም ሲሉ አይስተዋልም።በመሰረቱ፤ ጳውሎስ በአቴንስ ላሉ ሰዎች የነበረው መልዕክት ስለ አዳኙ ሳይሆን፤ ስለ ፈራጁ የሚናገር ነበር።

ሰዎች በኢየሱስ ፍርድ ፊት እንደሚቆሙ እውቀቱ ከሌላቸው፤የተለያየ አይነት ህይወት እንደሚኖሩ ልነግራችሁ አፈልጋለሁ።በዘመናዊ ክርስትና ውስጥ በጣም ቸልተኝነት እና ጥመት አለ፤ምክንያቱም ኢየሱስ አዳኝ ብቻ እንጂ ፈራጅ የሆነበትን እውነታ አልተጋፈጥንምና ነው። “እግዚአብሔር ዓለምን በጽድቅ የሚፈርድበት ቀንን ወስኗል” የፍርድ ጉዳይ ምንድ ነው? ጽድቅ ነው።

እንዴት ነው የኖርነው፤ምን አይነት ሰዎች ነበርን የሚለውን ይመለከታል።የምናምነው የሐይማኖት አስተምርዎ፤ዜግነት፤ማህበራዊ ሁኔታ. . . ጥያቄ አይደለም። አንድ የፍርድ ጉዳይ ብቻ አለ፤እርሱም ጽድቅ ነው።ዮሐንስ በመጀመሪያ መልዕክቱ ጽድቅ ያልሆነ ሁሉ ሐጢያት እንደሆነ ይናገራል። ጠማማነት ምንድ እንደሆነ ለማወቅ እንደመፈለግ ነው። እኔ የሒሳብ ባለሙያ አይደለሁም፤ነገር ግን ቀጥ ያለ መስመርን ላሳያችሁ እወዳለሁ፤ከመስመሩ የሚያፈነግጥ ማንኛውም ነገር ጠማማነት ነው።በአንድ ዲግሪ ወይም በ90 ዲግሪ ሊወጣ ይችላል፤ይሁን እንጂ ሁሉም ጠማማነት ነው። ጽድቅ ያልሆነ ሁሉ ሐጢያት ነው። በሥስተኛ ስፍራ ላይ የተቀመጠ የለም።

ዛሬ በርካታ ክርስቲያኖችን አስተውያለሁ፤ያሉት በሥስተኛ ምድብ ውስጥ ነው። ደህና፤ያ ጽድቅ አይደለም፤ነገር ግን ሐጢያት ነው።

ያ ምድብ በእግዚአብሔር አዕምሮ ውስጥ የለም። ጽድቅ ያልሆነ ሁሉ ሐጢያት ነውና።

በሐዋሪያት ሥራ 20 ጳውሎስ ከጠቅላላው አገልግሎቱ ታላላቅ ውጤቶችን ባስመዘገበበት በኤፌሶን በነበረው አገልግሎት የሰጠውን

መግለጫዎች እንመለከታለን።እሱ በኤፌሶን ስላሉ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች እየተናገረ ነው፤ምክንያቱም እሱ ትታቸው ሊሄድ ነውና፤

እንዲህ ይላቸዋል “ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንዳታዩ አውቃለሁ።” እርሱ ለእነዚያ ሰዎች የፍቅር መልዕክት እና ሃሳብ አለው።

በቁጥር 20–21 በኤፌሶን ስላለው አገልግሎቱ ይናገራል፤

“ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች ስንኳ አላስቀረሁባችሁም . . .”

ብዙ ጊዜ ይህንን ሐረግ አሰላስያለሁ፤ “አንዳች ስንኳ አላስቀረሁባችሁም” ሙሉውን እውነት ላለመስበክ አንድ መነሳሳት እንዳለ የሚጠቁም ነው፤ምክንያቱም በማሕበረሰብ ውስጥ የሚኖራችሁን ስፍራ የሚያሳጣችሁ ስለሚሆን ነው።በአንድ የኃይማኖት አስተምሮ ውስጥ የሚያገለግሉ ከሆነ፤በዚያ ኃይማኖት አስተምርዎ ውስጥ ያለዎትን ስፍራ

Tape No. B4152, N.Z.,
12/94

ያሳጣዎታል።በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ታዋቂ ከሆኑ፤ያንን በማህበረሰብ ውስጥ በሚኖርዎት እውቅና ላይ ዋጋ የስከፍልዎታል።ስለዚህ ጳውሎስ፤ "መልዕክት ከማስተላለፍ የሚያግደኝ ምንም አይነት ነገር ተጽዕኖ እንዳያሳድርብኝ ወሰንኩ፤ ይላል።

> ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሐንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች እየመሰከርሁ በጉባኤም በየቤታችሁም አወራሁላችሁና አስተማርኋችሁ እንጂ÷ ከሚጠቅማችሁ ነገር አንዳች ስንኳ አላስቀረሁባችሁም።

ይህን መልዕክት እወደዋለሁ፤የእርሱ መልዕክት በትልቅ ጉባኤ ውስጥም ሆነ በቤት ውስጥ አገልግሎት የሚቀየር አይደለም። ተመሳሳይ የሆነ መልዕክት ነበር። ያ ምን ማለት ነበር?

> ". . . ወደ እግዚአብሔር ዘንድ ንስሐንና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንን ለአይሁድና ለግሪክ ሰዎች እየመሰከርሁ"

መጀመሪያ የሚመጣው ምንድ ነው?እምነት ወይም ንስሀ? ንስሃ ነው። ንስሃ "እግዚአብሔር ሆይ፤አዝናለሁ። እኔ ሐጢያተኛ ነኝ፤የራሴን ህይወት ስመራ ኖሬአለሁ፤ይቅር በለኝ" በማለት ወደ እግዚአብሔር የሚደረግ ነው።ከዚያም እምነት ደግሞ ወደ ኢየሱስ የሚወስደን መንገድ ነው። "ኢየሱስ፤የእኔን ስፍራ እንደወሰድክ አምንሃለሁ።ለእኔ ብለህ በመስቀል ላይ ሞትክ፤ሐጢያቴን ሁሉ ወሰድክ።" በማለት በእምነት ወደ ፊቱ አንቀርባለን። ይሁን እንጂ ወደ እግዚአብሔር እውነተኛ ንስሃ ካልገባችሁ በስተቀር በኢየሱስ ላይ እውነተኛ እምነት ሊኖራችሁ አይችልም።

ተመልከቱ፤አዲስ ኪዳን ወጥነት ያለው ነው።ብዙ ጊዜ መልዕክቱን በሚገባ ባለመናገር፤ህዝብን በማሳሳት፤እውነተኛ ክርስቲያን መሆንን በተመለከተ ሐሰተኛ የሆነ ስሜትን በመፍጠር፤ቤተክርስቲያን ንስሃ ልትገባበት የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ አስባለሁ። ያለ እውተኛ ንስሃ እውነተኛ ክርስቲያን መሆን አይቻልም። ያለ ንስሃ እምነት የለምና።

መጽሐፍ ቅዱስ በማንኛወም ስፍራ የሚገኝ ሁሉም ሰው ንስሃ እንዲገባ ይናገራል። ለምን በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ሰዎች? ልትሉ

ትችላላችሁ፤እስቲ ከትንቢተ ኢሳይያስ መጽሐፍ መልስ ልስጣችሁ። ኢሳ 53:6 ይህን ይናገራል፤

እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤

አያችሁ፤ያ የእኛ ችግር ነው። ነፍስ አልደገልን ወይም ጣዖት አምልከን አናውቅም ይሆናል፤ወይም ምንም አይነት ነገር ሰርቀን፤ወይም ዋሽተን አናውቅም።ዳሩ ግን ሁላችንም አንድ ነገር አድርገናል፤ወደገዛ መንገዳችን አዘንብለናል።መንገዳችን የእግዚአብሔር አይደለም።የሐይማኖት አስተምርዎ ወይም ዘር የኋላ ታሪካችንን በተመለከተ

ያለን አንድ የጋራ ነገር ነው።የቆዳ ቀለማችን ምንም ይሁን ምንም ወደገዛ መንገደችን አዘንብለናል።

እንዲህ ይላል:

እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።

ሐጢያት የሚለው ጠንካራ ቃል ነው። ወደ ገዛ መንገዳችን ማዘንበል ማለት ምንድ ነው?ወደ ገዛ መንገዳችን ማዘንበል ማለት፤ሐጢያት ማለት ነው፤አምጽ ማለት ነው፤እንዲሁም እራሴን ከእግዚአብሔር በፊት አስቀድሜአለሁ ማለት ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ያለ ሰው ንስሃ እንዲገባ የሚጠይቀው። ምክንያቱም ሁላችንም ወደገዛ መንገዳችን አዘንብለናልና። ሁላችንም የራሳችንን ነገር በማድረግ እየተመላለስን ነው፤ራሳችንን ስናስደስት ኖረናል፤እግዚአብሔርን ከስዕሉ ውስጥ አስወግደናል።እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ "ንስሃ የምትገቡ ከሆነ፤ኢየሱስ ከሰራው ሥራ የተነሳ፤እቀበላችኋለሁ፤ይቅር እላችኋላሁ።" ያ የመጨረሻው መስመር ነው፤ንስሃ መግባት ነው።

ምህረት የምናገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤ሁልጊዜ የምንታመነው በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ነው።ከእግዚአብሔር ጸጋ ውጪ፤

ከመንፈስ ቅዱስ ስራ ውጪ፤ንስሃ መግባት እንችልም።ይህ በግልጽ በመዝሙር 80 ላይ ተጠቅሷል። ተመሳሳይ ሐረግ በመዝሙረ ዳዊት

ውስጥ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል።በማነበው እትም ውስጥ፤እንዲህ ይላል፤ቁጥር 3

አቤቱ÷ መልሰን÷ ፊትህንም አብራ÷ እኛም እንድናለን።

ነገር ግን "መልሰን" በሚለው ስፍራ ላይ የአብራይስጡ ትርጉም "እንድንመለስ እርዳን" ይለዋል። በሌላ አባባል፤ንስሃ እንድንገባ እርዳን ማለት ነው። ያ በቁጥር 3 ላይ ሦስት ጊዜ ተጠቅሷል:

አቤቱ÷ መልሰን÷ ፊትህንም አብራ÷ እኛም እንድናለን።

ቁጥር 7:

መልሰን÷ኛም እንድናለን።

ቁጥር 19:

አቤቱ÷ መልሰን÷እኛም እንድናለን።

ተረዳችሁ?እግዚአብሔር ካልቀየራችሁ በስተቀር ንስሃ ልትገቡ አትችሉም።ለወጥ የሚጀምረው ከእግአዚአብሔር ዘንድ

ነው።እግዚአብሔር ሊቀይረን ሲጀምር ያ በህይወታችን ያለ ትልቁ አጋጣሚ የሚሆነው ለዚህ ነው፤ምክንያቱም ራሳችንን በእንቢታ ነቅንቀን ከተመለስን፤ንስሃ ልንገባ አንችልም። ንስሃ ለመግባት በእግዚአብሔር ላይ የምንደገፍ ነን።

ሰቆቃው ኤርሚያስ ምዕራፍ 5፤21 እንመልከት። ሰቆቃው ኤርሚያስ በእግዚአብሔር ላይ በአመጻቸው በመቀጠላቸው የተነሳ በኢየሩሳሌም ላይ በደረሰው ጥፋት ምክንያት የተጻፈ የኤርሚያስ ለቅሶ ነው።እንዲህ ይላል፤ሰቆቃው ኤርሚያስ 5:21

በዚህ ትርጉም ውስጥ፤ "መልሰን" ይላል።ይህ ቃል በመዝሙረ ዳዊት 80 የተነገረው አይነት ተመሳሳይ ቃል ነው።

አቤቱ መልሰን፤እኛም እንመለሰለን።

መልሰን፤እንመለሳለን።ይህ በጣም፤በጣም ጠንካራ ሃሳብ ነው።እግዚአብሔር ካልመለሳችሁ በስተቀር ልትመለሱ አትችሉም። ለዚህ ነው በሁላችንም ህይወት ውስጥ ስሜት የሚነካ አጋጣሚ የሚሆነው።

በጦር ሰረዊት ውስጥ ጓደኛዬ የነበረ አንድ ወጣት ልጅ አውቃለሁ። ወደ ጌታ በመጣሁበት ጊዜ ብቸኛው ምስክር የነበረው እሱ ነበር። እሱ በህይወቴ የነበረውን ለውጥ ያውቅ ነበር።በኋላም በተመሳሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጀመርኩ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን እንዴት መምራት እንዳለብኝ ምንም ግንዛቤው አልነበረኝም ነበር፤ከየት እንደምጀምር አላውቅም ነበር፤ከአዲስ ኪዳን መጀመር እንዳለብኝ ተሰማኝ። ከየት ነው የምጀምረው? ብዬ ራሴን ጠየኩኝ፤ስለዚህ በምዕራፍ 1 ላይ ከሚገኘው ከኢየሱስ የዘር ግንድ ጀመርኩ።ቀጠልኩ፤እናም አራት ወይም አምስት የሚሆኑ የወታደር ጓደኞቼ ይካፈሉ ነበር።ይህ እንግዲህ ይሆን የነበረው በሰሜን አፍሪካ በሚገኘው ምድረ በዳ ውስጥ ነበር።ይህ ጓደኛዬ—በእውነቱ በጣም ጥሩ ጓደኛዬ ነበር—ሆኖም አንድ ቀን ወደ እኔም መጥቶ፤ "አዝናለሁ ጓደኛዬ፤ከዚህ በኋላ ወደ አንተ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አልመጣም" አለኝ። እኔም "ለምን አትመጣም?" አልኩት፤እሱም፤"ምክንያቱም ወደ አንተ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የምመጣ ከሆነ እንደምለወጥ አውቃለሁ" አለኝ። ይሁን እንጂ ከዓመታት በኋላ ፍጹም በተለየ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አገኘሁት። ድሮ ከማውቀው በጣም የተጎዳ ሰው ሆኖ ነበር።እንድረዳው ለመነኝ።የምችለውን ሁሉ አደረኩ።ሚስቱን በመርዳት ጌታን ተቀብላ እንድትድን ሆነች።እሱ በመጨረሻ ምን እንደሆነ አላውቅም፤ነገር ግን በህይወቴ ትልቅ ትምህርት ነው የሆነኝ። መመለስ በምትፈልጉበት ጊዜ መመለስ እንደምትችሉ ታስቡ ይሆናል። እንዲህ ልትሉ ትችላላችሁ፤ "እግዚአብሔር ሆይ፤አሁን በጣም ስራ በዝቶብኛል፤በኋላ ተመልሰህ ና።" በመሰረቱ ያንን ልታደርጉ አትችሉም።እሱ ሊመልሳችሁ በፈለገ ጊዜ ሊመልሳችሁ አልቻለም። እርሱ የንስሃ እድል እንደገና አይሰጥም ማለት አልችልም፤የእርሱ የመጨረሻ ምዕራፍ ምን እንደነበር አላውቅም።ነገር ግን ትልቅ ትምህርት እንደሆነኝ አውቃለሁ!

በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ደህንነትን እንዲቀበል በሚናገረው ጊዜ እኔ አልከሰስኩትም።እርሱ ደህንነትን በሚፈልግበት ጊዜ እግዚአብሔር አልተናገረውም። የእርሱ መጨረሻ ምን እንደነበር ማን ያውቃል።

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ለንስሃ አንድ አማራጭ ብቻ እንዳለ ይናገራል፤ይህም በሉቃስ 13 ውስጥ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት የኢየሱስ አገልግሎት ላይ ተጠቅሷል።

በዚያን ጊዜም ሰዎች መጥተው ጲላጦስ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር ስላደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች አወሩለት።

በግልጽ ለመነጋገር ጲላጦስ ደማቸውን ከመስዋዕታቸው ጋር ደባልቋቸው ነበር።ለመልካምነታቸው ይቆጠርላቸዋል ብላችሁ ታስቡ ይሆናል፤ኢየሱስ ግን በመልሱ እንዲህ ይላል፤

ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ስለ ደረሰባቸው ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስሉአችኋልን?
አላችኋለሁ፥ አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ።
ወይስ በሰሌሆም ግንቡ የወደቀባቸውና የገደላቸው እነዚያ አሥራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሁሉ ይልቅ በደለኞች ይመስሉአችኋልን? አይደለም፥ አላችኋለሁ፤
ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ።

ሁለት አማራጭ ብቻ አለ። ንስሃ መግባት ወይም መጥፋት። እነዚያ የኢየሱስ የራሱ ቃላት ናቸው።

እንግዲህ፤ንስሃ ወደ እምነት የሚወስድ መንገድ ነው ብለናል።እስቲ ትንሽ ስለ እምነት ባህሪ እንመልከት፤ከዚያም ወደሚቀጥለው ትምህርታችን እንሸጋገራለን።ሮሜ 10:17 አስቀድሜ የጠቀስኩላችሁ ክፍል ነው፤እንዲህ ይላል፤“እምነት ከመስማት ነው፤መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው።”ያ በጣም አስፈላጊ የሆነ መርህ ነው።እምነት፤በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሷል ማለት እምነት ሁልጊዜ የሚገኘው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ነው ማለት ነው።እምነት የሚመጣው ምንጩ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው፤እንድ ብቻ አትኩሮት አለው፤እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።አያችሁ፤በዘመናዊ ኢንግሊዝኛ መናገር እንችላለን፤ህክምና በሚሰጠኝ ዶክተሬ ላይ ትልቅ እምነት አለኝ። ወይም፤ በፖለቲካ ፓርቲ ላይ እምነት አለኝ፤ወይም በመድሃኒቶች ላይ ወይም የአመጋገብ ስርአት ላይ እምነት አለኝ።ያ ተገቢ ነው፤እነዚያን ቃላት መጠቀም ምንም ስህተት የለውም፤ ይሁን እንጂ ያ መንፈሳዊ የእምነት አጠቃቀም አይደለም። እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ነው።በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሰረተ ማንኛውም አይነት ነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት አይደለም።

እንግዲህ ዕብራውያን 11 የእምነትን ትርጉም አስቀምጧል። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስ አብራርቶ የስቀመጠው ብቸኛው ቃል እምነት እንደሆነ ላስብ አልችልም።በዕብራውያን 11:1 እንዲህ ይላል

እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ÷ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።

ስለዚህ፤በእምነት እና በተስፋ መካከል ሁበረት አለ።እምነት እንዳላቸው በሚያስቡ ጊዜ ተስፋ የሚኖራቸው በርካታ ሰዎችን አግኝቻለሁ።

እምነት እዚህ እና አሁን ነው፤ተስፋ ደግሞ የወደፊቱን የሚያስረዳ ነው።እምነት አንድ ፍሬ ነገር ነው፤አንድ እውን የሆነ ነገር አንድ ፍሬ

ነገር ይበላል። እምነት በልባችንም ያለ ነው።እምነትን መሰረት አድርገን ስለ ወደፊት ተገቢ የሆነ ተስፋ ሊኖረን ይችላል።ነገር ግን ተገቢ

በሆነ እምነት ላይ ያልተመሰረተ ማንኛውም ተስፋ በምኞት የተሞላ ሃሳብ ነው።
ነገር ግን እምነት በልባችን ያለ ነገር እንደሆነ በአዕምሯችሁ ያዙ።

ሮሜ 10:10 እንዲህ ይላል፤

> ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።

> መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በአዕምሮ የሚቀመጥ ሳይሆን በልብ የሚኖር እንደሆነ አስተውሉ።ጳውሎስ በመናገር ይቀጥላል፤

> ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና

በአዲስ ኪዳን፤ማመን በሥራ ላይ ያለ ቃል እንጂ አንድ ነገር ላይ የቆመ ነገር አይደለም።አንድ በማሰብ ችሎታ ስፍራን የሚይዝ አይደለም።አዲስ ወደሆነ ነገር የሚመራ በልባችን ያለ ነገር ነው። እምነት የእንቅስቃሴ ድርጊት ገላጭ የሆነ ቃል ወይም ግስ ነው።በእምነት እስከ ደህንነት እናምናለን።የላቀ እምነት ሊኖራችሁ ይችላል፤መቼም የሚቀየር አይደለም።ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምርዎች በአዕምሮአችሁ የማሰብ አቅም ይዛችሁ ነገር ግን ያልተለወጠ ህይወት ልትመሩ ትችላላችሁ።ነገር ግን በልባችሁ እምነት ሲኖራችሁ፤ወደ ደህንነት ይመራችኃል።

እምነት አሁን ነው፤ተስፋ ደግሞ የወደፊቱን የሚያስረዳ ነው።እምነት በልብ የሚገኝ ነው፤ተስፋ ደግሞ በአዕምሮ የሚኖር ነው። 1ኛ ተሰሎንቄ 5:8 ጳውሎስ ስለ ሁለቱም ይናገራል። እሱ የተጠቀመው ስዕል በጣም አስደናቂ ነው።1ኛ ተሰሎንቄ 5:8፡ እንዲህ ይላል፤

> እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን÷ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር፤

ሁለት አይነት የጦር እቃዎች እንዳሉ አስተውሉ።እምነት ጋሻ ነው። እንግዲህ ጋሻ የሚጠበቀው ምንድን ነው?ልብን ካላችሁ ትክክል ነው። ነገር ግን ተስፋ የራስ ቁር ነው።የራስ ቁር የሚከላከለው ምንድ ነው? ጭንቅላትን ነው ካላችሁ

ትክክል ነው።እምነት የሚኖረው በልብ ውስጥ ሲሆን ተስፋ ደግሞ የሚኖረው በአዕምሮ ውስጥ ነው።

እንግዲህ ተስፋ በጣም አስፈላጊ ነው፤ምክንያቱም ማንኛውም ክርስቲያን በጎ አሳቢ መሆን አለበት። አሉታዊ አሳቢ ከሆናችሁ፤በእውነት እምነታችሁን አየካዳችሁ ነው።እኔ ተስፋን፤በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመስርቶ በእምነት መልካምን ነገር የሚጠበቅ፤ብዬ ልገልጸው እችላለሁ።እውነተኛ አማኝ የሆንን ሁሉ መልካምን የመጠበቅ እምነት አለን። ምክንያቱም በዚህ ህይወት ውስጥ ምንም ቢከሰት፤ከኢየሱስ ጋር ለዘለዓለም ልንሆን እንሄዳለን።ያ ተስፋችሁ ከሆነ፤ልትደበሩ ትችላላችሁ፤ልታዝኑ ትችላላችሁ፤ነገር ግን ተስፋ አትቆርጡም፤ምክንያቱም ተስፋ አላችሁና፤በእምነት ላይ የተመሰረተ ተስፋ አላችሁ።

እንግዲህ ስለ እምነት ተጨማሪ መግለጫዎችን ለማግኘት ወደ ዕብራውያን 11 እንመለስ።ይህ አስደናቂ 11ኛው የዕብራውያን ምዕራፍ፤ታላቅ የሆነ የእምነት ምዕራፍ ነው።

ዕብ 11:3 እንዲህ ይላል፤

ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን።

እምነት ከማይታየው ነገር ጋር እንደሚያገናኛችሁ ድልድይ መሆኑን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። እምነት በምናየው ላይ የተመሰረተ

አይደለም።

እምነት ከሚታየው ዓለም ስሜት ባሻገር ወደማይታየው ዓለም ይወስደናል።

እንዲሁም ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮ 5:7 እንዲህ ይላል፤

በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና።

አስተውሉ፤እነዚህ አማራጮች ናቸው።በማየት ስትመላለሱ፤ማመን አያስፈልጋችሁም።ማመን የሚያስፈልጋችሁ ማየት በማትችሉ ጊዜ ነው።ስለዚህ ጳውሎስ በእምነት እንመላለሳለን ይላል።በምናምነው እንጂ በምናየው አንመላለስምና።

ኢየሱስም በአላዕዛር መቃብር አጠገብ ለማርታ እንዲህ አላት፤

ኢየሱስ፦ ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዪ አልነገርሁሽምን? አላት።

ስለዚህ መጀመሪያ የሚመጣው የትኛው ነው? እምነት ካላችሁ ትክክል ነው። በርካታ ሰዎች "ደህና፤የማምነው፤ስመለከት ነው" ይላሉ። አይደለም፤ ያ ትክክል አይደለም፤ምክንያቱም በምትመለከቱ ጊዜ ማመን አያስፈልገችሁምና። ማመን የሚያስፈልገን ማየት በማንችልበት ጊዜ ነው። በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና። "እኔ የማምነው መየት ከቻልኩ ብቻ ነው"የሚሉ በርካታ ሰዎችን አግኝቻለሁ። ነገር ግን ያ ትክክል አይደለም። ማመን አያስፈልገችሁም። ማመን የሚያስፈልጋችሁ ማየት በማትችሉበት ጊዜ ነው። በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና።

እንዲሁም እኔ በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የግሪክ እና የአብራይስጥ ቋንቋዎች ልነግራችሁ እወዳለሁ፤እምነት በቅድሚያ የሐይማኖት አስተምርዎ

ጉዳይ አይደለም፤የባህሪ ጉዳይ እንጂ።በወንጌላውያን አስተሳሰባችን ስህተት ሰርተናል።ስለ እምነት ስናውራ የሐይማኖትን

አስተምርዎ በአዕምሮ የማሰብ ችሎታ እንደመያዝ አድርገን እንናገራለን።በመጀመሪያ እምነት የሐይማኖት አስተምርዎ ጉዳይ ሳይሆን

የባህሪ ጉዳይ ነው።ይህ በአብራይስጡ ኤማኑ(*emanau*)፤በግሪኩ ደግሞ ፒቶስ ተብሎ የተቀመጠው ነው።

ሁለቱም ትክክለኛነት፤ታማኝነት፤እና መሰጠት ማለት ናቸው።

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤"ነገር ግን እናንተ በፊተናዎቼ ከእኔ ጋር ጸንታችሁ የኖራችሁ ናችሁ፤"

ያ እምነት ነው። እምነት ከኢየሱስ ጋር ጽንዶ የሚኖር ነው። ለእንድ ሰው ግላዊ መሰጠት ነው።

በምንመሰክር ጊዜ እምነት ሊቀ ካህን ከሆነው ኢየሱስ ጋር ያገናኘናል። ዕብራውያን 3:1 እንዲህ ይላል፤

የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤

አስታውሱ።ይህ በጣም በጣም አስፈላጊ ነው። ኢየሱስ የእምነታችሁ ሊቀካህን ነው። እሱ የእናንተ ሊቀ ካህን ነው።እናንተ ዝም ያላችሁ እንደሆነ፤እርሱ ሊቀ ካህናችሁ ሊሆን አይችልም። ለዚህ ነው እምነታችሁን መመስከር አስፈላጊ የሚሆነው።

ዕብራውያን 4:14 እንዲህ ይላል፡

እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።

እንመሰክራለን፤እንፈተናለን፤ነገር ግን እምነታችንን አጥብቀን ደግሞ እንይዛለን።አጥብቀን በያዝን ቁጥር፤ኢየሱስ ሊቀ ካህናችን ይሆናል።ዳሩ ግን በዕብራውያን 10 ወደ ተጨመረ ደረጃ ይወስደናል። ዕብራውያን 10:21 እንዲህ ይላል፤

> በእግዚአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ስላለን÷ . . . *[ቁጥር 23:]* የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፤

ከእምነት ወደ ተስፋ እንደሄድን አስተውሉ።በእምነት ላይ የተመሰረተ ተስፋ አለን። እምነታችንን እንናገራለን፤እንዲሁም አሁን ደግሞ ተስፋችንን እንመሰክራለን። ቃሉ ያለ መናወጥ ይላል። እንደዚያ ሲናገር ምን ታስባላችሁ? ያለመናወጥ ብሎ ለምን ተናገረ? እምነታችንን አጥብቀን እንያዝ ለምን አለ? ምክንያቱ በርካታ የሆነ ተጻጻሪ ሃይላት እምነታችን ለማስጣል ስለሚዋጉን ነው፤በርካታ ውጊያዎች ሊወጉን ወደ እኛ ስለሚመጡ ነው፤በርካታ ነገሮች ተስፋ ሊያስቆርጡን እና እምነታችንን ዝቅ ሊያደርጉን ስለሚፈልጉን ነው።ይህ የቁርጠኝነት ጦርነት ነው። ይህ የጽናት ጦርነት ነው።

በመጨረሻም እንድ ነገር ልነግራችሁ ያስፈልጋል፤በጽናት፤እምነት ይፈተናል።ያልተፈተነ በእምነት በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ የለውም።ኢየሱስ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን ይናገራል፡

> ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ÷ ተገላናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን÷ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኩል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ።

ያ የተፈተነ እውነተኛ እምነት ነው።በጥንት ጊዜ በእሳት ተፈትኖ ያልወጣ ወርቅ ዋጋ አይኖረውም ነበር።ያልተፈተነ እምነት በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ዋጋ የለውም። እስቲ አንድ ጥቅስ ከያዕቆብ መጽሐፍ ልስጣችሁ፤ ያዕቆብ 1:2–4:

ወንድሞቼ ሆይ÷ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ÷ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቊጠሩት
ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።

ፍጹም እና የተዘጋጀችሁ መሆን ትፈልግላችሁን? ጽናት ፍጹም ሥራ እንዲሆን ፍቀዱ። ጴጥሮስ በአንድ ስፍራ ላይ እንዲህ ይላል፤

. . . ይልቅ አብልጦ የሚከብር የተፈተነ እምነታችሁ÷ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ÷ ለምስጋናና ለክብር ለውዳሴም ይገኝ ዘንድ አሁን ለጥቂት ጊዜ ቢያስፈልግ በልዩ ልዩ ፈተና አዝናችኋል።

ምናልባት እስካሁን ያልተናገርኩትን በአንድ የመጨረሻ ቃል ልናገር፤ጽናትን ለመማር አንድ መንገድ ብቻ አለ።ይህ ምን እንደሆነ ማወቅ ትፈልጋላችሁን? መጽናት ነው። ያ ትክክል ነው።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ።